

ለ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት PK3 እና PK4
የትምህርት ዘመን 2027-28

ዲስትሪክቱ የ PK እድሜ ማብቂያዎችን ለሚያሟሉ ነዋሪዎች በህዝብ እና በህዝብ ቻርተር ትምህርትቤቶች ውስጥ ነጻ የቅድመ መዋለ ህጻናት (PK) ትምህርት አገልግሎቶችን ያቀርባል። ለየትኛውም የትምህርት አመት ብቁ ለመሆን፡-

- ተማሪዎች ለPK3 ለማመልከት እስከ ሴፕቴምበር 30 ድረስ 3 አመታቸው መሆን አለበት
- ተማሪዎች ለPK4 ለማመልከት እስከ ሴፕቴምበር 30 ድረስ 4 አመታቸው መሆን አለበት
- ተማሪዎች ለመዋዕለ ህጻናት ለማመልከት እስከ ሴፕቴምበር 30 ድረስ 5 አመታቸው መሆን አለበት

ቤተሰቦች በMy School DC ውስጥ በሚሳተፉ ትምህርት ቤቶች ለሚቀርቡ የቅድመ መዋዕለ ህጻናት ፕሮግራሞች ለማመልከት የMy School DC ማመልከቻን መጠቀም አለባቸው።

- በአካባቢዎ ትምህርት ቤት ያለውን ፕሮግራም ጨምሮ፣ DCPS የቅድመ መዋዕለ ህጻናት 3 እና የቅድመ መዋዕለ ህጻናት 4 ፕሮግራሞች የእርስዎን የ DCPS የአካባቢ ቅድመ መዋዕለ ህጻናት ፕሮግራም ለማግኘት School Finder (http://find.myschooldc.org) ይጎብኙ፤ እና
- በህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ላይ የሚገኙ የቅድመ መዋዕለ ህጻናት ፕሮግራሞች

ቤተሰቦች በMy School DC ማመልከቻ ላይ እስከ 12 ትምህርት ቤቶች ድረስ ማመልከት ይችላሉ። ይሁን እንጂ፣ ምንም የእጣ ውድድር ወይም የመጠበቂያ ዝርዝር አቅርቦት ዋስትና የለም።

እንዲሁም ዲስትሪክቱ በማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች (CBOዎች) በኩል ለነዋሪዎች ከፍተኛ ጥራት ያለው የቅድመ መዋዕለ ህጻናትን ያቀርባል። ስለዲስትሪክቱ ከፍተኛ ጥራት ማህበረሰብ አቀፍ የቅድመ መዋዕለ ህጻናት ፕሮግራሞች የበለጠ ለማወቅ። ማህበረሰብ አቀፍ የቅድመ መዋዕለ ህጻናት ፕሮግራሞች የህዝብ ትምህርት ቤት እጣ አካል አይደሉም።

እስከ ማርች 1፣ 2027 ያመልክቱ

- **የቤተሰብ መለያ ያዘጋጁ።**
- **የMy School DC ማመልከቻዎን ለመሙላት የሚፈልጉትን መረጃ ሁሉ ይሰብስቡ።**
  ሁሉም የሚያስፈልጉት መረጃዎች ከሌሉዎት ማመልከቻውን ማስገባት አይችሉም። የዚህን መረጃ ማስፈንጠሪያ ለማግኘት የQR ኮዱን ይቃኙ።
- **በMy School DC ማመልከቻዎ ላይ ትምህርት ቤቶችን ያክሉ እና እርስዎ በሚፈልጉት ቅደም ተከተል ደረጃ ይስጧቸው።**
  ትምህርት ቤቶችዎን ደረጃ የሰጡበት ቅደም ተከተል ከትምህርት ቤቶች ጋር ሊዛመዱ የፈለጉበትን ቅደም ተከተል እንድናውቅ ያስችለናል፤ እንደ ወንድም እና እህት ወይም የዝውውር ምርጫዎች ላይ ብቁ መሆን ያሉ ማንኛውንም ምርጫዎች አይነካም።
- **ማመልከቻዎን እስከ ማርች 1 ቀን ያስገቡ።**
  ማርች 1 ቀን ከመድረሱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ያስገቡትን ማመልከቻ ማስተካከል ይችላሉ። የትምህርት ቤት ደረጃዎችን እስከ ማርች 12 ቀን ከቀኑ 5 p.m. ድረስ ማዘመን ይችላሉ።

ከማመልከትዎ በፊት

- **ዝርዝር ያዉጡ።**
  School Finder (http://find.myschooldc.org) ተጠቅመው ትምህርት ቤቶችን በአድራሻ፣ በክፍል እና በፕሮግራም አይነት (ለምሳሌ ሞንተሶሪ፣ ሁለት ቋንቋ፣ እና ሌሎችም) ይፈልጉ። እንዲሁም በዚህ መሳሪያ ወደ ትምህርት ቤት የመጓዝ እድልዎን ማሳየት ይችላሉ። ማስታወሻ፡- በተመለከቷቸው ትምህርት ቤቶች የእጣ ውድድር ወይም የመጠበቂያ ዝርዝር አቅርቦት ላይ ምንም አይነት ዋስትና ስለሌለ ሊከታተሏቸው በሚፈልጉት ሚፈልጓቸው ትምህርት ቤቶች ሁሉ ያመልክቱ። እስከ 12 ማመልከት ይችላሉ!

- **ትምህርት ቤቱን መለያዎችይመልከቱ።**
  የትምህርት ቤት መለያዎች ስለ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት መሰረታዊ መረጃን ያሳያሉ እናም እርስዎ የክፍት ቤት መርሃ ግብራቸውን ማየት ይችላሉ። ማመልከቻ የወሰዱበትን ውጤቶች፣ እንዲሁም በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙትን መቀመጫዎች ብዛት ያለፉ የእጣ መረጃዎችን፣ በውጤቶች ጊዜ የተጠባባቂ ዝርዝሩን ርዝመት እና የመጠበቂያ ዝርዝሩን እንቅስቃሴ የሚያሳይ ማስታወሻ ይያዙ። የዚህን መረጃ ማስፈንጠሪያ ለማግኘት የQR ኮዱን ይቃኙ።
- **EdFEST፣ የትምህርት ቤት ዝግጅቶች፣ እና ክፍት ቤቶች ላይ ይሳተፉ።**
  ምርጫዎችዎን ለማጥበብ እንዲረዱዎት በቀጥታ ለሚፈልጓቸው ትምህርት ቤቶች ጥያቄዎችን ይጠይቁ። የዚህን መረጃ ማስፈንጠሪያ ለማግኘት የQR ኮዱን ይቃኙ።
- **አውታረ መረቦችዎን ይጠቀሙ።**
  እርስዎ ስለሚያመለክቱባቸው ትምህርት ቤቶች እውቀት ካላቸው ሰዎች (ለምሳሌ፦ ጎረቤቶች፣ ጓደኞች፣ የትምህርት ቤት አማካሪዎች) ጋር መነጋገር ጠቃሚ ነገር ነው።
- **የደረጃ አሰጣጥዎን ይወስኑ።**
  የመጨረሻውን የትምህርት ቤቶች ዝርዝርዎን እርስዎ በመረጡት ቅደም ተከተል ያስቀምጣሉ። ዝርዝርዎን በዚህ ቅደም ተከተል ደረጃ መስጠት አስፈላጊ ነው። የእርስዎ ተዛማጅ ትምህርት ቤት ከላይ ባስቀመጡት ትምህርት ቤቶች የተጠባባቂ ዝርዝር ላይ ብቻ ያገኛሉ።

በወረቀት ላይ ማንበብ ይፈልጋሉ? ሁሉንም የተጠቀሱ ማስፈንጠሪያዎች ለማግኘት እዚህ ይቃኙ

ጠቃሚ፦ DCPS በቅድመ መዋዕለ ህጻናት 3 እና በቅድመ መዋዕለ ህጻናት4 ፕሮግራሞች
በአካባቢ ያለ ትምህርት ቤት ተማሪው ከመዋዕለ ህጻናት - 12ኛ ክፍል በሚኖርበት ቦታ ላይ የመማር መብት ያለው የDCPS ትምህርት ቤት ነው። **ይሁን እንጂ፣ "የመገኘት መብት" በቅድመ መዋዕለ ህጻናት 3 ወይም በቅድመ መዋዕለ ህጻናት 4 ላሉ ልጆች አልተስፋፋም እናም የእጣ መዛመድ ወይም ጠባቂ ዝርዝር አቅርቦት ዋስትና የለውም።** ቤተሰቦች ተማሪያቸውን በአካባቢ የቅድመ መዋዕለ ህጻናት 3 ወይም የቅድመ መዋዕለ ህጻናት 4 ፕሮግራማቸው ላይ ለማስመዝገብ ከፈለጉ፣ ያንን ትምህርት ቤት በMy School DC ማመልከቻቸው ላይ ካሉት 12 ምርጫዎቻቸው ውስጥ አንዱ መርጠው በጣም በሚወዱት ቅደም ተከተል ደረጃ መስጠት አለባቸው። የቅድመ መዋዕለ ህጻናት 3 ወይም የቅድመ መዋዕለ ህጻናት 4 አመልካቾች በአካባቢያቸው ባለ ትምህርት ቤት "የአካባቢ ውስጥ" የእጣ ምርጫ ይሸለማሉ እና፣ በምዝገባም ወቅት፣ በMy School DC ማመልከቻ ላይ የገባውን የአሳዳጊው አድራሻ ላይ ያለውን የነዋሪነት ማረጋገጫ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

ለቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት 3 ወይም ለቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት 4 እያመለከቱ ነው? ከታች ያሉ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ያስቡ፦

- የቀንዎ መዋቅር ምንድን ነው? ለምሳሌ፣ የጨዋታ ጊዜን፣ የእንቅልፍ ጊዜን ያካትታሉ?
- ልጄ ሽንት ቤት ለመጠቀም መሰልጠን አለበት/አለባት? በመጸዳጃ ቤት ስልጠና ላይ የእርስዎ ፖሊሲ ምንድን ነው?
- ልጄ ከቀን-ውሎ እንክብካቤ/ሔድ ስታርት ወደ ቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት እየተሸጋገረ/ች ነው። ልጄ ሽግግሩን ሲያደርግ/ስታደርግ ምን አይነት ድጋፍ ይሰጣሉ?
- ልጄ ግለሰባዊ የቤተሰብ አገልግሎት እቅድ (IFSP) አለው/ላት። ወደ ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ለመሸጋገር ከእኔ እና ከልጄ ጋር እንዴት ይሰራሉ?
- የእርስዎ የቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት (PK3-PK4) የክትትል ፖሊሲ ምንድን ነው?